የሰ/መ/ቁ. 48269

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሸረፈዲን አብደላ - ጠበቃ አብዶ መሐመድ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ማርታ አሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ ተከሳሽ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የአመልካች የስር ክስ ይዘት ባጭሩ፡- አቶ አህመድ ኢሳ ኪይሮ የተባሉ ግለሰብ በተጠሪ ባንክ ሚዛን ተፈሪ ቅርንጫፍ ታህሣሥ 16 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. በ25/12/2006) በመቅረብ ብር 145,860.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር) ለአመልካች ገቢ በማድረግ ማስተላለፋቸውን፣አመልካች ይሕንን ገንዘብ ለማውጣት ገንዘቡን እንዲከፍል ለታዘዘው አየር ጤና ቅርንጫፍ ቢሄዱ ገንዘቡን ለሌላ ግለሰብ እንደከፈለ በመግለጽ ክፍያው ለአመልካች ሊፈፀምላቸው የማይችል መሆኑን የገለፀ መሆኑን በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክፍያው ይፈፀም ይችል ከነበረበት ከጥር 01 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድና ከተለያዩ ወጪዎች እና ኪሳራዎች ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አመልካች በገንዘቡ ላይ መብት ወይም ጥቅም ስለሌላቸው ክስ ለመመስረት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ክፍያው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል የፈፀሙ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ክፍያውን የፈፀመው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል በመሆኑ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ክፍያውን የፈፀመው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል ነው ተብሎ ገንዘብ ላኪው ግለሰብ እንኳ ቀርቦ እንዲመሰክር ሳይደረግ ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ወስዶ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ በመክፈሉ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ መሆኑ ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ጥር 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካችም በ11/06/2002 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረጉት ምክንያት ገንዘቡ በስህተትና በሐሰት ለሌላ ሰው ተከፍሎብኛል የሚለውን መሆኑን፣ተጠሪም ገንዘቡ በላኪው ግለሰብ በተላለፈው መሰረት ገንዘቡ ለተላከለት ሰው ከፍያለሁ ብሎ የሚከራከር መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ከፍያለሁ የሚለው ከአመልካች ጋር ተመሳሳይ ስም ላለው ሰው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር በመከተል ስለመሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ ተጠሪን ከክሱ ኃላፊነት ነፃ ማድረጉን ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ ለተላከለት ሰው በትክክል የማድረስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ባንኩ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው ካላደረሰ ኃላፊነት የሚኖርበት ሲሆን ኃላፊነቱ የሚከተለው ግን ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል መቅረቱ ወይም ራሱ ባንኩ መጭበርበሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር መከተሉን የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካች ገንዘቡን ከባንኩ የወሰዱት ግለሰብ ባንኩን ያጭበረበሩት ስለመሆናቸውን በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ገንዘቡን ለአመልካች ላኩ የተባሉት ሰው ለማስረጃነት አመልካች የቆጠሯቸው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ አመልካች የስር ፍርድ ቤት